ሐምሌ 30 ቀን 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**10ኛ መደበኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ውሳኔዎች**

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 10ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. ምክር ቤቱ በቀዳሚነት የተወያየው የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣንን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን በቀረበው ደንብ ላይ ሲሆን የፌዴራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 የነዳጅና ኢነርጂ ጉዳዮችን የሚመራ ተቋም በአዲስ መልክ ያቋቋመ መሆኑን ተከትሎ ባለስልጣኑ ሴክተሩን በብቃት መምራት የሚያስችል ስልጣንና ተግባር እንዲኖረው የሚያስችል ደንብ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠል ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የብሔራዊ የክፍያ ስርአት አዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ ቀደም ሲል የነበረውን አዋጅ ማሻሻል ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት አገራችን በጀመረችው አጠቃላይ አገራዊ የሪፎርም አጀንዳ ማዕቀፍ ውስጥ የክፍያ አገልግሎት ሰጪዎችን ተሳትፎ በማስፋት የክፍያ ስርአቱን ውጤታማነት፣ አስተማማኝነትና ተወዳዳሪነት ለማጎልበት፤ ገበያዉ አበክሮ የሚፈልጋቸዉንና በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረጉትን ለዉጦች፣ ዕድገቶችና መሻሻሎች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የክፍያ ስርዓታችንን ማዘመን ይቻል ዘንድ የማሻሻያ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

3. ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለጤናው ዘርፍ ዘላቂ የልማት ግቦች ፕሮጀክት እንዲሁም ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር የምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በተፈቀዱ ብድሮች ማጽደቂያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ነው፡፡ ከጣሊያን መንግሥት የተገኘው ብድር የ10 ሚሊዮን ዩሮ ሲሆን ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ደግሞ 400 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ነው፡፡ ምክር ቤቱም ብድሮቹ ከ1 ፐርሰንት ያነሰ ወለድ የሚከፈልባቸው፣ እስከ 12 ዓመታት የሚደርስ የችሮታ ጊዜ ያላቸው እና በ38 ዓመታት ተከፍለው የሚጠናቀቁ መሆናቸውን ይህም ከአገራችን የብድር ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ይጸድቁ ዘንድ ረቂቅ አዋጆቹን ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ወስኗል፡፡

4. ቀጥሎ ምክር ቤቱ ውይይቱን ያደረገው የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ ሲሆን በካፒታል እጥረት ምክንያት የስራ እንቅስቃሴያቸው የተዳከሙ ድርጅቶች ተጨማሪ ካፒታል ለማሰባሰብ ከሚሸጡት አዲስ አክሲዮን የሚገኝ ገቢን ከግብር ነጻ ማድረግ የሚኖረውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደዚሁም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65 (2) ኢኮኖሚያዊ፤ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች መኖራቸው ሲታመን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ድንብ በማውጣት አንድን ገቢ ከግብር ነፃ ሊያደርግ እንደሚችል በተደነገገው መሰረት ረቅቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

5. ሌላው ምክር ቤቱ የተወያየበት አጀንዳ ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የቀረበ ረቂቅ ደንብ ነው፡፡ ወደ አገር በሚገቡ በተወሰኑ ምርቶች ላይ አነስተኛ ቀረጥ በመጣል በሚገኘው ገቢ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማስፋፋት፤ በመጠገን እና በማሻሻል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስቻል ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በደንቡ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

6. በመጨረሻ ምክር ቤቱ የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ የተወያየ ሲሆን የመንግስትና የግል አጋርነት አሰራር በዋናነት የግል ሴክተሩን እውቀት፣ ክህሎትና የፋይናንስ አቅም በመጠቀም የህዝብ አገልግሎት መስጫ መሰረተ ልማቶችን ጥራትና ደረጃ ለማሳደግና ለማስፋፋት፣ ስራው በግልጽ ውድድርና ፍትሃዊነት እንዲፈጸም ለማድረግ እንዲሁም በአገራችን ማክሮ ኢኮኖሚ ሂደት የሚታዩ ተግዳሮቶችን በተለይም የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግርን እንዲታደግ ለማድረግ እንደ አንድ የልማት ፋይናንስ አማራጭ ዘዴ በመውሰድ የተቀየሰ የህግ ማዕቀፍ ነው፡፡ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማሳከት ከተለያዩ ሀገራት መንግሥታት ጋር በሚኖር የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አማካኝነት እንዲሁም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ለአገር እና ለሕዝብ ጠቀሜታ ያላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦችን በቀጥታ ድርድር መተግበር ጠቃሚ መሆኑ የታመነበት ቢሆንም አሁን በስራ ላይ ያለው አዋጅ ይህን አሰራር የማይፈቅድ በመሆኑ አዋጁን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ የማሻሻያ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብአቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መርቶታል፡፡

//